## ትምህርት 10

### ሕያው እንጀራ (The Living Bread)

በተለምዶ የጌታ ራት ተብሎ ስለሚጠራው ጉዳይ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ርዕሶች አንዱ መሆኑን የሚታወቅ ነው። ትምህርቱ የሚያተኩርባቸው 6 አብይ ነጥቦች ስላሉ ይህን ማዕድ በምንወስድበት ጊዜ ልናተኩርበት የሚገባው ምንም ሳንተው በሁሉም ነጥቦች ላይ ነው። ይህን ትምህርት ለማዘጋጀት ያነሳሳኝና በተለይ ያተኮርኩበት ክፍል የምንካፈለው የጌታ ማዕድ ኃይል ያለው ወይም የሌለው መሆኑን በሚለይልን በ5ኛው ነጥብ ላይ ነው።

ሕያው እንጀራ ለመውሰድ በምንሰባሰብበት ወቅት ማድረግ ያለብን ነገሮች

1. **ጌታን ማሰብ/ የሆነልንን ሁሉ ማስታወስ፡-** ሉቃ 22፡19-20፣ 1ቆሮ 11፡17-23-26-32፣ ማቴ 26:26-28

**ለመታሰቢያዬ አድርጉት፡-** ሉቃ 22፡19፣ እኔ ከጌታ የተቀበልሁትን ለእናንተ አስተላልፌያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት ሌሊት እንጀራን አንሥቶ [24] ከባረከ በኋላ ቈርሶ፣ “ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ለመታሰቢያዬም አድርጉት” አለ።

እኛ የሰው ዘሮች በእግዚአብሔር የተደረጉልን ብዙ ነገሮች ከጊዜ በኋላ እየረሳን መሄድ አንዱ ዋነኛ ችግራችን ነው። ጌታን የምናስበው የጌታ ማዕድ በምንወስድበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁል ጊዜ ማሰብ/ማስታወስ ያለብን፤ ምን ጊዜም ልንረሳው የማይገባ ሆኖ ሳለ፣ ጌታ በብዙ ነገር እንደ ምንባክን ስለሚያውቅ ተሰብስበን ማዕዱን በአንድነት በምንወስድበት ጊዜ እንኳ እንድናስበው ነግሮናል። ስለዚህ እስከ መስቀል ሞት ድረስ የከፈለልን ታላቅ የመከራ ዋጋ መቼውም ቢሆን እንዳንረሳው ልንጠነቀቅ ይገባል።

ይህ የሕያው እንጀራ (የጌታ ራት) ቅዱስ ስርዓት የደነገገው ራሱ ጌታ ስለሆነ ከእርሱ የተነሳ የሚገኘውን ጸጋ እስከፈለግን ድረስ ሳናደርገው ልንተወው የሚቻል አይደለም፣ (ዮሐ 6፡53።)

ዮሐ 6፡56-57 "Eats, Drinks, Feeds" የሚሉት ቃላት በሕይወት ዘመናችን ሁሉ መደረግ ያለበት ቀጣይነት ያለው እንጂ ለተወሰነ ጊዜ ተወስዶ የሚቋረጥ አለመሆኑን ያሳያሉ። በሐዋሪያት ዘመን መጀመሪያ በየዕለቱ በኋላም በየሳምንቱ በቤታቸው ያደርጉት የነበረ ነው። ሐሥ 2፡42-46፣ 20፡7።

ለዚህ የጌታ ማዕድ የምንጠቀምባቸው ነገሮች ዳቦ/እንጀራ/ቂጣ፣ በአሁኑ ጊዜ ከምን የተሰራ መሆን እንዳለበት በአብያተ-ክርስቲያናት የተደረሰበት ስምምነት ስለሌለ፤ ምግብ ሊሆን ከሚችል ማንኛውም የስንዴ፣ የገብስ፣ የጤፍና አጃ ዝርያዎች የሚሰራና እርሾ የሌለው ሲሆን፣ የምንጠጣው የወይን ጭማቂ/ከወይን የተሰራ መሆን ይችላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን የግዴታ እርሾ የሌለው መሆን ነበረበት:: (እርሾው የሚያመለክተው ጥቂት እርሾ ብዙ ሊጥ እንደ ሚያቦካ ትንሽ የሚመስል ኃጢአት መላ ሕይወትን የሚያረክስ መሆኑን ነው)።

**ጌታ ኢየሱስን የምናስበው የዋለልን ውለታና እኛን በሰራነው ኃጢአታችን ይጠብቀን ለነበረ የከፋ መከራ ለማዳን ምን ያህል ታላቅ ዋጋ እንደ ከፈለ መዘርዘር ትልቅ መጽሐፍ ሊወጣው የሚችል ቢሆንም ቢያንስ የሚከተሉትን ነገሮች ብናስብና ብናስታውስ መልካም ነው።**

**1.ሀ.** ጌታ ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ሳለ ሰው ሆኖ በሰው ማኅጸን ተጸንሶ በከብቶች ግርግም ተወልዶ፣ በሕጻንነት ዕድሜው ሄሮድስ ሊያስገድለው ስለ ፈለገ ከሰሜናዊው እስራኤል በገሊላ ከምትገኘው ናዝሬት በመነሳት ወደ ግብጽ መሰደዱን። በዚህ ጊዜ የተጓዘው መንገድ ርዝመት ቢያንስ 700 ኪሎ ሜትር ስለሚሆን ያን ያህል ርቀት በበረሃ ለመጓዝ ሳምንታት እንደ ፈጀበት ይገመታል። ለ3 ዓመት ተኩል ከቤተሰቡ ጋር በስደት አገር በአስቸጋሪ ኑሮ ከቆየ በኋላ ከግብጽ ሲመለስም ያንኑ ርቀት ምድረ-በዳ ባለው መንገድ መጓዙን።

**1. ለ.** አገልግሎት ሊጀምር ሲል 40 ቀንና ሌሊት በምድረ-በዳ በመጾምና በመጸይ መራቡና መድከሙን፡፡ ብዙ ጊዜ ቀኑን ሙሉ ለሕዝቡ ወንጌል በመስበክና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደሆነ ገልጾ በማስተማር፣ ልዩ ልዩ ፈውስና ከእስራት ነጻ የማውጣት ሥራ ማከናወኑን፤ የሞተን አስነሳ፣ ሞቶ የተቀበረን ከቀናት በኋላ አስነስቶ በህይወት በማኖር ብዙ ተአምራዊ ተግባራት መፈጸሙን፡፡ እንደዚህ ቀኑን በሙሉ እየሰራ ከቦታ ቦታ እየተጓዘ ደክሞ ቢውልም ሲመሽ ወደ ተራራ በመውጣት በብርድ ሌሊቱን ሁሉ ሲጸልይ ያድር የነበረ መሆኑን፡፡ የመለኮት ሙላትና ክብር ያለው ሆኖ ሳለ ለፈጠረው ሰው አገልጋይ ሆኖ የደቀ-መዛሙርቱን እግር ማጠቡን፡፡ ከሰው ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግና ፈቃድ ሁሉ ምንም ሳያዛባ በመፈጸም እግዚአብሔር አብን ሙሉ በሙሉ የሚያረካ የጽድቅ ሕይወት መኖሩን፣

እንከን የማይወጣለት የጽድቅ ትምህርት በማስተማር ተጽፎ እንዲቀመጥልን ማድረጉን፡፡ በጌተሰማኔ ሊገድሉት በሚፈልጉት ጠላቶቹ ከመያዙ በፊት ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የሚደርስበትን ታላቅ ስቃይና መከራ አውቆ እጅግ ተጨንቆ ላቡ እንደ ደም ነጠብጣብ መፍሰሱን፡፡ ጌታ ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ሳለ ሆነ ብሎ ራሱን ዝቅ አድርጎ በሰው አምሳል ተገኝቶ ከላይ የተዘረዘረው ሁሉ ውርደት፣ መከራና ሥቃይ የተቀበለውና የጽድቅ ሥራ ያከናወነው በእርሱ የሚያምን የሰው ዘር ሁሉ የእርሱ ጽደቅ ሆኖ እንዲቆጠርለት ለማስቻል መሆኑን፡፡

**1.ሐ.** እጅግ ብዙ በሆነው መልካም ተግባሩ ፈንታ፣ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት እንደ ሚታረድ በግ፣ እንደ አደገኛ አመጸኛ ተይዞ/ታስሮ ምሽት በጭለማ መነዳቱን፡፡ በአይሁድ ሃይማኖት መሪዎችና ተባባሪዎቻቸው ጋኔን ያደረበት እብድ (ዮሐ 10፡20፣) አሳች (ሉቃ 23፡2፣) ወንጀለኛ (ዮሐ 18፡30፣) መባሉን፤ ያፌዙበትን፣ የተፉበትን፣ የደበደቡትን፣ ልብሱን የገፈፉትን፣ በጅራፍ ያስገረፉትን፤

በመጨረሻም በእንጨት መስቀል ላይ ሰቅለው መልካም ያደረገባቸው እጆቹና እግሮቹ መስቀሉ ላይ በምስማር ቸንክረው፣ ለመዘባበቻ ራሱ ላይ የሾህ አክሊል ደፍተውበት፣ ጎኑን በጦር ወግተው ስለ ገደሉት እንደ ሰው በስጋ ሞቶ መቀበሩን፡፡ እርሱ አንዳች ኃጢአት የሌለበት ሆኖ ሳለ ኃጢአታችንና እርግማናችንን ከኛ ወስዶ በመሸከሙ ለእኛ የተገባውን እጅግ አሰቃቂ መከራና ሰቆቃ አድርሰውበት የኛ እርግማንና የዘላለም ሞት ቅጣት ፍርዳችንን እርሱ መቀበሉን፡፡

**1.መ.** እነዚህን ውለታዎቹን ሁሉ በማስታወስ እርሱን የምናደንቅበት፣ የምናመሰግንበትና በእርሱ ደስ የምንሰኝበት ነው፡፡ እርሱ ምን ያህል እንደ ወደደን አይተን እኛም ለእርሱ ያለን ፍቅራችንን ለማሳየት ደስ በሚያሰኘው ሁኔታ እንደ ፈቃዱ ለመኖር ልባችንን የምናዘጋጅበት ነው፡፡ ጌታ የሰራልን ታላቅ ስራ ማስታወስ ኃጠአት በማድረግ እንዳንቀጥል በማንቃት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመኖር የመነሳሳት ግዴታ ያለብን መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በሌላ ጎኑ እግዚአብሔር ለኃጢአታችን ስርየት ከክርስቶስ ኢየሱስ መስዋዕትነት በስተቀር ሌላ መፍትሔ አጣ ማለት፡-

> የኃጢአት ዋጋና መዘዙ ምን ያህል የከፋና ታላቅ፣ የዘላለም ሞት ከምናስበው በላይ አሰቃቂና አስጨናቂ መሆኑን ያስገነዝባል፤ ቀላል ቢሆን ኖሮ ጌታ ይሄን ያህል ታላቅ ዋጋ አይከፍልም ነበር፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔር ኃጠአትን ምን ያህል አጥብቆ እንደሚጠላ፣ እንደሚጠየፍ፣ እንደሚያሳዝነውና ምን ያህል የበረከት እጁን ሊዘረጋልን የሚከለክል መሆኑን አውቀን እንድንጠነቀቅ የሚያነቃን ደወል ነው፡፡

**2. ማወጅ 1ቆሮ 11፡26፣** *"ይህን እንጀራ በምትበሉበት ጊዜ፣ ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ፡፡"*

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ መሆኑን፣ ስለኃጢአታችን በኛ ፈንታ ሞቶ በተቀበረ በሶስተኛው ቀን ከሙታን መነሳቱንና ወደ ሰማይ አርጎ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ መሆኑን በዘመናችን ሁሉ

ለእግዚአብሔር ህዝብ እርስ በርስ፣ ለመንፈሳዊ ፍጥረታት ማለትም ለቅዱሳን መላእክትና ለክፉ መናፍስት፤ በውጭ ላሉት ላልዳኑትም የምናውጅበት ነው።

**3. የወደፊቱን መጠበቅ** ***ሀ.****1ቆሮ 11:26፣ "ይህን እንጀራ በምትበሉበት ጊዜ፣ ይህንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ።"*

እርሱ ለኛ ለሚያበዛው ጸጋ ቀጣይ ስራ ስላለው ሊያከብረን ከእርሱ ጋር አብረን እያየነው እንድንኖር ሊያደርገን እንደገና ተመልሶ የሚመጣ መሆኑን የምናስታውስበት፣ መምጣቱን የምንናፍቅበትና በሙሉ ተስፋ የምንጠባበቅበት ነው። ወደኋላ የምናስታውሰው መስቀሉ ለወደፊት የምናየው ዳግም ምጽአቱን ነው። ወደ ፊት አንድ ቀን በጌታ ማዕድ ፊት ለፊት ከእርሱ ጋር አብረን ሆነን አብረን እንድንበላ እንጠብቃለን። ማቴ 26፡ 29፣

ለኃጢአታችን መሰስዋዕት ሆኖ የታረደልን በግ ጌታ ኢየሱስና የቤተ-ክርስቲያን ሰርግ ከተፈመ በኋላ፣

ራእይ 21፡3-4፣ ደግሞም እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ፤ "እነሆ፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ በሰዎች መካከል ነው፤ እርሱ ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ አምላካቸውም ይሆናል። 4 እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ልቅሶ ወይም ሥቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው ሥርዐት ዐልፎአልና።" የሚለው ቃል ተፈጽሞ በአይናችን እናያለን።

ጌታ ይመጣል! በቶሎ ይመጣል! በድንገት ሳይታሰብ ይመጣል፣ እኛም ጌታ ሆይ አሜን ና እያልን እንጠባበቃለን፤

**የጌታን ሰውነት በተመለከተ**

**4. የጌታን ማዕድ ለመካፈል በሚያስችል (የተገባን በሚያደርገን) ሕይወት ለመገኘት መስራት** 1ቆሮ 11፡27-32፣

***ሀ****. 1ቆሮ 11:27፣ "ማንም ሰው ያልተገባው (Greek word- አናክሲዮስ/unworthy) ሆኖ ሳለ፣ የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታንም ጽዋ ቢጠጣ፣ የጌታን ስጋና ደም በማቃለሉ ይጠየቅበታል፤"* (የግሪክና የእንግሊዝኛ ቃሉ በቅንፍ ውስጥ አስፍሬዋለሁ)

*ይህ ቃል የተገባን ሆነን ሳንገኝ የጌታን ማዕድ መካፈል እንደሌለብን ያስረዳል። ጌታ ኢየሱስ የጌታን ስጋና ደም እንዲወስዱ የፈቀደላቸው ለእርሱ የተለዩት ደቀመዛሙርት እንጂ እርሱን በመፈለግ ለመጣ ሕዝብ ሁሉ አልነበረም። ከ12ቱ አንዱ የነበረው የአስቆሮቱ ይሁዳ እንኳ ከእርሱ ተለይቶ ከወጣ በኋላ መሆኑ ይታመናል።*

*አንድ ሰው የጌታን ሕብስትና ጽዋ ለመውሰድ ያልተገባው የሚያደርገው በኃጢአት እየተመላለስ ያለ ከሆነ ወይም ንስሃ በመግባት ከአንግዲህ ይህን ኃጢአት አላደርግም ብሎ የገባውን ቃል በማፍረስ መልሶ መላልሶ ኃጢአት ማድረግ የሚቀጥል ሆኖ ሲገኝ ነው። ንስሃ ከገቡ በኋላ ያንኑ ኃጢአት ደጋግመው የሚደርጉ ከሆነ ከልብ የሆነ ንስሃ አለመግባትን ያሳያልና።*

1ቆሮ 11፡18 *በቆሮንቶስ አማኞች መካከል መለያየት ነበረ። መለያየት እንዲከሰት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ብዙ ናቸው። የምንናገረውና የምናደርገው ነገር ሁሉ መለያየት ለመፍጠር ምክንያት እንዳይሆን እያንዳንዱ ራሱን እየመረመረ ማስወገድ ወይም ተገኛኝቶ በመነጋገር መፍታት አለበት፤ በጌታ የህይወት መስዋእትነት የተዋጁትን የአካሉ ብልቶች ምድራዊ በሆነ የሀብት/የንብረት፣ የዕውቀት/የትምህርትና የቁመና እንዲሁም የኑሮ ደረጃቸው ምንም ያህል ቢለያይ ሁሉንም በእኩል በማክበር ፈንታ መናቅ፣ በማቅረብ ፈንታ ማግለል/ማራቅ፣ በመውደድ ፈንታ መጥላት፣ አበላልጦ ማየት ካለ ማረም። ሁላችንም እኩል በጌታ ስራና ጸጋ*

የዳንን ስለሆነ ሰውን ሁሉ በውጫዊ ገጽታው ሳይሆን ክርስቶስ የከፈለለትን ታላቅ ዋጋና የሰጠውን ክብር ማየትና በአክብሮት ማስተናገድ/መያዝ ነው።

በቤተ-ክርሰስቲያን ውስጥ በሚሰራ የተለያየ ስራ እርስ በርስ በመተሳሰብ የጋራ ጥቅም በሚያስገኝና ጌታን በሚያከብር ሁኔታ በመስራት ፈንታ የግል ጥቅምና ክብር ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ ማከናወን እያደር በአባላቱ መካከል መከፋፈል እና መለያየት እንዲከሰት በር የሚከፍት ስለሆነ ጥንቃቄ ማድረግ።

1ቆሮ 10:14፣ 19-21 ከጣዖት አምላኪዎች ጋር መተባበር በተመለከተ ከእግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ውጪ ሌሎች አማልክት የሚያመልኩት ከሚካፈሉት መብልና ጽዋ መካፈል በእግዚአብሔር የተጠላ መሆኑን አውቆ በድረጊታቸው ከመተግበር መቆጠብ።

አንዳችን ስለሌላው ሰው ልናውቀው የምንችለው እየፈጸመው ያለ የኃጢአት ዓይነት ጥቂት ነው። ሁሉን የሚያውቀው እግዚአብሔር አንዳች የሚሰወርበት ነገር ስለሌለ ሁሉም ጉድለታችን ስለሚያውቅ፤ መራቅና መጠንቀቅ ያለብን ከላይ ከተጠቀሱት ኃጢአት ዝርዝር ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ኃጢአት መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

**ለ. ራስን መመርመር፡-** *1ቆሮ 11:28፣ "ስለዚህ ማንም ሰው ይህን ህብስት ከመብላቱና ይህንንም ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት ራሱን መመርመር (Greek word- ዳኪማትዞ/Examine) አለበት። ...31 ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር።"*

ማንኛውም አማኝ የጌታን ኅብስትና ጽዋ ከመብላቱና ከመጠጣቱ በፊት ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ አለበት። ዝግጅቱም እንደ እግዚአብሔር ቃል እየኖሩ መሆን አለመሆኑን በመመርመር ራስን በመፈተሽ፣ የፈጸሙት ኃጢአት ካለ ከልብ የሆነ ንስሀ ገብቶ የአግዚአብሔርን ምህረት በመጠየቅ ከዚያ በኋላ ያንን ኃጢአት ማድረግ ከተዉ ራስን አዘጋጁ ማለት ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ የራሱን አካሄድ በእግዚአብሔር ቃል በመመርመርና እውነተኛ ንስሀ በመግባት ራሱን ማዘጋጀት አለበት። መናዘዝና መተው የማይፈልጉት አብሮ እንዲቆይ የሚፈቀድለት ማንኛውም ኃጢአት እያለ በንስሃ ሳያስወግዱ የጌታ ራት መውሰድ ውጤቱ አደገኛ ነው። 1ቆሮ 1:31፣ ቆላ 3:5፣ 1ተሰ 2:12

**ሐ. የጌታን ሥጋና ደም ምን እንደሆነ ለይቶ ማወቅ (የጌታ ሥጋና ደም ዋጋ ክቡርነት መለየት)፡-**
*1ቆሮ 11:29፣ 32፣ "ማንም ሰው የጌታን ስጋ ምን መሆኑን ለይቶ ሳያውቅ (ዲያክሪኖ/discerning) የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታን ጽዋ ቢጠጣ በራሱ ላይ ፍርድን ያመጣል። ከእናንተ መካካል ብዙዎች የደከሙትና የታመሙት አንዳንዶችም የሞቱት በዚህ ምክንያት ነው።...ነገር ግን ጌታ በሚፈርድብን ጊዜ እንገሥጻለን፤ ይኸውም ከዓለም ጋር አብረን እንዳንኰነን ነው።"*

የምንቀበለው የጌታ ማዕድ በውጭ ገጽታው እንደምናየው ተራ ዳቦና ወይን ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት እጅግ የከበረ ዋጋና ኃይል ያለው ነው። የጌታን ሰውነት ክቡርነት ሳይለዩ በወሰዱት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ኃይል ስላለው የመንፈሳዊ ኃይል መድከም፣ የጤንነት መጓደል/መታመም፣ ያለጊዜው መሞት አስከትሏል። ጌታ በእኛ ኃጢአት ምክንያትያን ያን ያህል ታላቅ መስዋዕትነት መክፈሉን እያወቅን አሁንም ባልተገባ ሁኔታ በመገኘት ስጋና ደሙን በመውሰድ እርሱ የሰራልንን ታላቅ ስራ አቅልሎ መመልከት ስለሆነ የዲስፕሊን እርምጃ ያስከትላል። ጌታም ራሳቸውን ሳያዘጋጁ የጌታን ኅብስትና ጽዋ በወሰዱት ላይ ቅጣት የሚፈጽመው በጌታ ከማያምነው የዓለም ሕዝብ ጋር በአንድነት የዘለዓለም ሞት እንዳይፈርድብን በንስሃ መመለስ እንድንችል ነው። ዕብ 12:5-11

**5. *መመገብ/መብላት*** (ሜቴሆ-Partake) ፡- 1ቆሮ 10:21-31፣ ዮሐ 6:30-51፣ 53-58፣ ተቀብለን የምንበላው ኅብስትና ወይን እንዴት ልናየው/ልናውቀው ይገባል። ለጌታ ማዕድ የምንጠቀምባቸው ነገሮች

ዳቦ/እንጀራ/ምግብ ሊሆን ከሚችል ማንኛውም ጥራጥሬ የሚሰራና እርሾ የሌለው ነው፣ የምንጠጣው የወይን ጭማቂ/ከወይን የተሰራ መሆን ይችላል፡

ዮሐ 6፡25፣ ጌታ ኢየሱስ 5000 ሰዎችን በአምስት ትንንሽ እንጀራና በ2 ትንንሽ ዓሳ መግቦ በማጥገብ ብዙ (12) መሶብ እንዲተርፍ ባደረገ ጊዜ ከዚያ ምግብ የበሉ ሰዎች በማግስቱ እርሱን ፍለጋ ወጥተው ከባህሩ ማዶ ሲያገኙት፣ "ረቢ መቼ ወደዚህ መጣህ" አሉት። ጌታ ኢየሱስም "የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ታምራዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም፣ ለሚጠፋ እንጀራ አትስሩ" አላቸው።

ለምንድነው ታምራዊ ምልከቶችን ስላያችሁ አይደለም የምትፈልጉኝ ያላቸው። እንዲህ ያለበት ምክንያት ጌታ ያደርጋቸው የነበሩት ድንቆችና ታምራዊ ስራዎች፤ ይመጣል ተብሎ የተስፋ ቃል የተነገረለት መሲህ ሲመጣ ያደርጋቸዋል ተብለው የተተነበዩ፣ እርሱ መሲሁ መሆኑን ከሚመሰክሩ ማረጋገጫ ማስረጃዎች ዝርዝር ውስጥ ስለ ነበሩ ነው። እርሱም የፈለገው ሕዝቡ መሲሁ መሆኑን እንዲያውቁት ስለ ነበር ነው። ጌታ ወደ ምድር ከመጣባቸው ዓላማዎች አንዱ የራሱን ማንነት ማስተዋወቅ ነበርና። ነገር ግን ይፈልጉት የነበሩት ሰዎች ጌታ ኢሱስ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው መሲሁ መሆኑን ስላወቁ ሊከተኩት ወስነው አልነበረም።

ከዚህ በኂላ ጥያቄና መልሱ ሁሉ በአሁኑ ጊዜ የጌታ ራት ስለሚባለው ሆኖ ቀጠለ። ይህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምዕራፍ በላቀ ሁኔታ ስለ ምንካፈለው ህብስትና ጽዋ በተከታታይ ሰፊ ማብራሪያ የሰጠበት ነው።

**በአንድነት ተሰባስበን በኅብረት የምንካፈለው ኅብስት፤ ጌታ ምን ብሎ ነው በዚህ ስፍራ ባስተማረው ቃሉ የጠራው?**

1. ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር (ለማይጠፋ) ምግብ ስሩ። ቁ 27
2. አውነተኛ እንጀራ................................. ቁ 32
3. የእግዚአብሔር እንጀራ .......................... ቁ 33
4. ከሰማይ የሚወርድ (የወረደ) እንጀራ............ ቁ 33፣ 41፣ 50፣ 58
5. ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ................... ቁ 51፣
6. ሕይወት የሚሰጥ እንጃራ........................... ቁ 33
7. የሕይወት እንጀራ.................................... ቁ 35፣ 48
8. ሰው እንዳይሞት የሚበላው (ሞትን የሚከለክል) እንጀራ.. ቁ 50

(8 ጊዜ የእንጀራ ዓይነት ስም፣12 ጊዜ የተደጋገም የዘላለም ሕይወት ያለውና የሚሰጥ እንጀራ ብሎታል)

**ስለ ሥጋና ደሙ የተናገረው**

9. ለዓለም ሕይወት እንዲሆን የምሰጠው ሥጋዬ.... ቁ 51
10. የሰውን ልጅ ስጋና ደሙ............................. ቁ 53
11. ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ.................. ቁ 54፣ 56
12. ሥጋዬ እውነተኛ ምግብና ደሜ አውነተኛ መጠጥ.. ቁ 55

**ስለ መብላት እና መጠጣት**

13. ሰው እንዳይሞት ይበላው ዘንድ ከሰማይ የሚወርድ እንጀራ ቁ 50 (ጌታ ነው ከሰማይ የወረደው)

14. ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል........... ቁ 51

15. የሰውን ልጅ ስጋውን ካልበላችሁ፣ ደሙን ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ህይወት የላችሁም ቁ 53

16. ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው ቁ 54

17. ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በርሱ እኖራለሁ...ቁ 56

18. እኔም ከአብ የተነሳ በሕይወት እንደምኖር የሚበላኝም ከእኔ የተነሳ በሕይወት ይኖራል ቁ 57

ይህ የጌታ ማዕድ "የጌታ ራት" ተብሎ በመጠራቱ ቅሬታ ባይኖረኝም ከእነዚህ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጌታ ራሱ ከሰጣቸው ስሞች በአንዱ ቢጠራ ኖሮ ስለ ጌታ ማዕድ ኃይል ያለው መሆን የበለጠ ግንዛቤ ይሰጥ ነበር ብዬ አምናለሁ።

**ስለዚህ መያዝ ያለብን ቢያንስ 3 ነገሮች አሉ**

5.1. ጌታ ኢየሱስ ከሐዋሪያቱ ጋር ለመጨረሻ ጊዜው የተመገበው የብሉይ ኪዳን የፋሲካ ራት፣ የጌታ ራት ነው፤ ይህን ሥርዓት ያከናወነበት/የመሰረተበት ዕለት፤ ጌታን ሊገድሉ ያሴሩ ሰዎች ሊይዙት በሚመጡበት ቀን ነበር። (1ቆሮ 11:23)

በዚህ ራት መጨረሻ ገደማ ተጠቅመውበት ከቀረው ኅብስት ቆርሶ ጽዋውንም አንስቶ ለሐዋሪያቱ ሲሰጥ ከቃል ጋር ነበር። ጌታ ከቃል ጋር ለሐዋሪያቱ ከሰጣቸው ኅብስትና ጽዋ ግን አልተካፈለም። ለምን ቢባል፣ የራሱ ሰውነት ሕይወትና ኃይል ያለው ስለነበር። ሐዋሪያቱ ከተመገቡት የብሉይ ኪዳን ፋሲካ ራትና ቆርሶ ሬማ በመናገር ከሰጣቸው ኅብስት ጋር ሲነጻጸር የተለያዩና የተራራቁ ነገሮች ናቸው። የመጀመሪያውን የበሉ የስጋ መሞት ከሚያደርስ አጥፊ ድነዋል። የኋለኛውን የበሉና የሚበሉ ግን በዋናነት ከዘለዓለም ሞት በመዳን የዘላለም ሕይወት አግኝተዋል/ያገኛሉም። (ዮሐ 6፤48-50) ጌታ በእነዚህ 23ቱ ክፍሎች የተናገረው የራሱ ሰውነት ስላለው ኃይል ነው እንጂ ጌታ ስለ ተመገበው ራት አይደለም።

ጌታ ኢየሱስ የተናገረው ቃል እውነት ስለሆነ ከተራ ቁጥር 1-18 በተዘረዘሩት 23 ጊዜ የደጋገመው መለኮታዊ ቃል ሁሉ እውነት ነው። ይህም እውነተኛ ቃል የሚገልጸው የጌታ ኢየሱስ ሁለት ሰብዕና (አምላክ-ሰው) አጣምሮ የያዘ ሰውነት የዘለዓለም ሕይወት ኃይል ያለው መሆኑን ነው። ለሐዋሪያቱም ሊሰጥ የፈለገውና የሰጠው ይህንኑ የዘላለም ሕይወት ያለውን ነበር። የምንወስደው የጌታ ኅብስትና ጽዋ 23 ጊዜ ደጋግሞ የዘላለም ሕይወት ኃይል ያለው መሆኑ የሚገልጹ ዓረፍተ-ነገሮችና ሐረጎች ተናግሯል። ስለዚህ እውነተኛ የሆነው ቃሉን አምነን መቀበል አለብን። በእምነት የዘላለም ሕይወት እንዳገኘን በስጋና ደሙም የዘላለም ሕይወት ኃይል እናገኛለን ማለት ነው (አንደ ምናገኝ ማመን አለብን)።

5.2. ዮሐ 6:61-63 ከጌታ አፍ የወጣው ቃል (ሬማ) "እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው" (መንፈስም ሕይወትም ነው) ያላቸው። እዚህም ላይ ልብ ልንለው የሚገባው ነገር "መንፈስ ነው ሕይወትም ነው" ያለው ቆርሶ የሰጣቸውን ኅብስት ሳይሆን የተናገራቸውን ቃል መሆኑን ነው።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ለማውጣት በኮሬብ ተራራ ሙሴን በተገናኘው ጊዜ ከ ዘጸ 3:4-22 ባለው ስፍራ ለሙሴ ወደ ሕዝቡ እንዲሄድና የተናገረውን ሁሉ ነግሯቸው ሕዝቡን ነጻ የማውጣቱ ስራ እንዲጀምር ወደ ሙሉ ምዕራፍ የሚደርስ ቃል ቢናገረውም ሙሴ እሺ ብሎ በመሄድ አምኖ "ቃል" በመናገር ስራውን በመጀመር ፈንታ እንደገና ምዕራፉፍ 4 ላይ "ባያምኑኝስ፣ ቃሌን ባይቀበሉስ" ... በማለት መሄድ አለመፈለጉን አሳየ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴ እንዲያምን የሚያግዝ ነገር መጠቀም ጀመረና በእጅህ የያዝሃት በትር መሬት ላይ ጣላት አለው። ለብዙ ጊዜ በእጁ የነበረችው ተራ በትር እግዚአብሔር

በተናገረው መሰረት ሲጥላት እባብ ሆነች፣ በል እጅህን ዘርጋና ጅራተዋን ያዛት አለው። እንደተናገረው ጅራትዋን ሲይዛት እባብዋ ተለውጣ በእጁ ላይ በትር ሆነች።

ጌታ ኢየሱስ ተመግበውት ከቀረው ቆርሶ የሰጣቸው ኅብስት ልክ ከላይ በተገለጸው መሰረት ማመናቸውን እንዲያግዝ ወይም የእምነት ማስተላለፊያ እንዲሆን ነው እንጂ የሚሰራና የዘላለም ሕይወት ኃይል ያለው በተናገረው ቃል ነው።

ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃል (ሬማ) ኃይል ያለው ነው። ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃልና በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል የአግዚአብሔር አገልጋይ/ሕዝብ አምኖ ሲናገረው የእምነት ቃል ይባላል። የእምነት ቃልም ኃይል አለው። ጌታ ስለዚህ ጉዳይ ያስተማረውን አንድ ስፍራ እንመልከት፦

ሉቃ 17፥6 “ጌታም፣ “የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ፣ ይህን ሾላ፣ ‘ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ተተከል’ ብትሉት ይታዘዝላችኊል” አላቸው።”

እምነት ቢኖራቸውም እምነታቸው ውጤት ያለው ነገር እንዲያስገኝን በአፋቸው መናገር ነበረባቸው። እምነት እያላቸው ሾላው አጠገብ ደርሰው ዝም ብው ቢቆሙ ምንም ውጤት አይገኝም ማለት ነው። ወይም አንድ የወንጌል አገልጋይ በአጋንንት የተያዘ ሰው አቅርበውለት እባክህ እርዳው ቢሉት፣ አገልጋዪ እምነት ቢኖረውም ጭጭ ብሎ በታመመው ሰው አጠገብ ቢቆም ምንም መልካም ውጤት ስለማያገኝ ክፉውን መንፈስ በእምነት ድምጽ በማውጣት ለቆት እንዲሄድ ማዘዝ አለበት።

ትኩረታችን ኅብስቱና ወይኑ ምንድናቸው ወይም ምን ይሆናሉ በሚለው ላይ መሆን የለበትም። እነርሱ እምነታቸውን ለማውጣት/to release faith/ እንዲያግዙ ብቻ የተጠቀመባቸው ነገሮች ናቸው።

በየጊዜው የጌታ ራት በሚሰጥበት ወቅት አገልጋዩ የጌታን ማዕድና ጽዋ በእጁ ይዞ ከሰማይ የወረድህልን ሕያው እንጀራ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለኛ ህይወት የሚሰጥ ምግብና መጠጥ እንዲሆንልን ይሄ ስጋህና ደምህን ስለሰጠኸን እናመሰግንሀለን ብሎ ከጸለየ በኋላ ለምዕመናን ሲሰጥ በእምነት ጌታ ራሱ እንደ ተናገረው "እንካ/እንኩ ይህ የጌታ ኢየሱስ ስጋና ደም ነው" በማለት የእምነት ቃል መናገር ይገባዋል።

የጌታ ራት ከአገልጋዩ ስንቀበል እኛም "ይሄ ስጋዬ ነው፣ ይሄ ደሜ ነው" እያለ ጌታ ኢየሱስ ራሱ እንደሰጠን በመቁጠር ቃሉን (ሬማውን) በእምነት መያዝ አለብን። ማንኛውም የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን አዎንታዊ ለውጥ የሚያመጣው አምነን ስንቀበለው ነው። ስለዚህ እኛም ስንወስደውም አምነን የእምነት ቃል በመናገር መሆን አለበት። ይሄ ለኔ የታረደው የፋሲካዬ በግ የጌታ ኢየሱስ ስጋና ደም የዘላለም ሕይወት የሚሰጠኝ እንጀራና መጠጥ ነው፣ ብለን መንፈሱና ህይወቱ እንዳለበት አምነን ነው መቀበል ያለብን። የምንወስደው የጌታ ስጋና ደም በእርግጥ የኢየሱስ መንፈስና ሕይወት ያለበት እኛንም ከቃሉ የተነሳ የርሱን መንፈስና ሕይወት ኃይል ተቀባዮች የሚያደርገን መሆኑን ማመን አለብን።

ስለዚህ ጌታ የዘላለም ሕይወት ያለው ኃይሉ በስጋውም ሰጠን፣ በደሙም ሰጠን፣ በቃሉም ሰጠን፣ በመንፈሱም ወይም በእምነትም ሰጠን፤ ልዩነቱ ባንረዳውም እንኳ እርግጠኞች መሆን ያለብን፣ ይህን ስርዓት ስናከናውን የጌታ የዘላለም ሕይወት ኃይል በኛ ውስጥ አልፎ የሚሰራው ነገር ያለ መሆኑን እንጂ ከንቱ ስርዓት ደጋግሞ የሚያሰራን አለመሆኑን ነው።

አንድ አማኝ መንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ከሕይወቱ የሚጠርገውን ይጠርጋል፤ የሚያድሰውን ያድሳል፣ ያበረታታል፣ ያነቃቃል። ይሄ አንድ ጊዜ ብቻ የሚከናወን ተግባር ሳይሆን በየጊዜው ይደጋገማል። ስጋና ደሙን በምንወስድበትም ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚሰራው ነገር አለ።

5.3. የጌታ ኢየሱስ ስጋና ደም በአዎንታዊና አሉታዊ ጎን የሚሰራ ኃይል ያለው ነው እንጂ በአሉታዊ ጎን ብቻ የሚሰራ አለመሆኑ።

1 ቆሮ 11፡29-30 “ማንም ሰው የጌታን ስጋ ምን እንደሆነ ለይቶ ሳያውቅ የጌታን ሕብስት ቢበላና የጌታን ጽዋ ቢጠጣ በራሱ ላይ ፍርድን ያመጣል፡፡ ከእናንተ መካከል ብዙዎች የደከሙትና የታመሙት፤ አንዳንዶችም ያንቀላፉት (የሞቱት) በዚህ ምክንያት ነው፡፡"

ከዚህ በላይ የሰፈረው ጥቅስ የሚያረጋግጠው የጌታ ኅብስትና ጽዋ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ የከበረ ዋጋና ኃይል ያለው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ኃይል አሉታዊ ብቻ ሳይሆን አዎንታዊ ተጽዕኖ በሕይወታችን ላይ ማሳደር የሚችል ነው፡፡

ይህ ማእድ ሳይገባቸው በወሰዱት ላይ የመንፈሳዊ ኃይል መድከም፣ የጤንነት መጓደል/መታመም፤ ያለ ጊዜው መሞት የሚያደርስ ኃይል ካለው በተገቢው ሁኔታ ራሳቸውን አዘጋጅተው ለወሰዱት የተለያየ የበረከት ኃይል እንዳለው የሚያሳይ አንዱ ማስረጃ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ**፡- ጌታ ኢየሱስ ራሱ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስተምር የተወሰኑ ሰዎች ስላልተረዱት "ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤ ማንስ ሊቀበለው ይችላል?" በማለት ጌታን ከመከተል ወደ ኋላ በመመለስ እርሱን መከተላቸውን የተዉ ስለሆነ አሁንም የመረዳት ልዩነት መኖሩ የሚደንቅ አይደለም (ዮሐ 6፡60-66)፡፡ በክርስትና እምነት ትምህርት ውስጥ መሰረታዊ የእምነት ምሰሶዎች ተደርገው የሚታዩ የእምነት መግለጫዎች አሉ፡፡ የቤተ-ክርስቲያን አባላት በእነዚህ መሰረታዊ አስተምህሮዎች እስከ ተስማሙ ድረስ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ የተለያየ አተረጓጎም/አረዳድ ቢኖራቸውም በአንድነት ጌታን ማምለካቸውን ይቀጥላሉ እንጂ በአንዳንድ መሰረታዊ ባልሆኑ የትምህርት አርእስት ላይ የተለያየ አረዳድ መከሰቱ እያደር እየተረዱት ስለሚመጡ ለመለያየት በር መከፈት/ምክንያት መሆን የለበትም፡፡

ስእያንዳንዱ በራሱ አእምሮ እንደ ተረዳው ይዞ በጌታ መንፈስ ቅዱስ የተገኘውን የመንፈስ አንድነት በመጠበቅ ማስቀጠል ተገቢ መሆኑን እንዘንጋ፡፡ በዚህ ትምህርት እንደ ተገለጸው የምንወስደው የጌታ ስጋና ደም ኃይል እንዳለው የማይናገሩ አገልጋዮችም ሆኑ አማኞች ሌሎችን ለማሳት ብለው ሐሰተኛ ትምህርት ያስተምራሉ ማለት ስላልሆነ በክፉ ዓይን ማየት አይገባም፡፡ የጌታ ስጋና ደም ቃሉ እንደ ሚናገረው ኂይል አለው ብሎ የሚያምን ኃይሉን በመቀበል ተጠቃሚ ይሆናል ማለት ነው፡

**6. ከጌታ ጋር ግንኙነታችንን የምናድስበትና በስሙ ያመንን ሁሉ በእርሱ አማካኝነት አንድነታችን/ኅብረታችን እንዳይሳሳ የምናጎለብትበት ነው**፣ (ግሪክ- ኮይኖኒያ/communion/share) ዮሐ 6፡53-56 (1ቆሮ 10፡16-17) *ሥጋውን የበላንና ደሙን የጠጣን ሁላችን በእርሱ እንኖራለን*፣ የክርስቶስ ኢየሱስ የአካሉ ክፍሎች አባላት ተደርገናል፡፡ ከእርሱ ጋር እንደ አንድ ሰውነት መተሳሰር አግኝተናል፡፡ ብዙዎች ብንሆንም እርስ በራሳችንም በአንዱ በክርስቶስ ኢየሱስ አካል አንድ ሆነናል፡፡ ራሷ ክርስቶስ የሆናት የአንዲት መንፈሳዊት ቤተ-ክርስቲያን (አካሉ) ክፍል ሆነናል፡፡

ዮሐ 6፡56 *ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ*፡፡ የጌታ ማዕድ መወሰድ ያለበት በጌታ ያመኑት (በአንድ አጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን አባል የሆኑት) በአንድነት በተሰበሰቡበት ነው፡፡ እርስ በርሳችን በፍቅር፣ በአክብሮትና በመተሳሰብ የምንያያዝበት ነው፡፡ ጌታ ስለ መሰባሰባችን በ1ቆሮ 11፡17፣ 18፣ 20፣ 33፣ 34፣ አምስት ጊዜ ጠቅሶታል፡፡ (ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በተናጠል ለታመሙና ለመሞት ለተቃረቡ ሰዎች፣ በሰርግ ስፍራ ለሙሽራውና ሙሽሪቱ፣ እንዲሁም ለጥቂት የቤተ-ክርስቲያን አባለት ብቻ የሚሰጡበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ይሄ ከቃሉ አይስማማም)

ጌታን ከተከተሉ በርካታ ደቀመዛሙርት ጀምሮ በሐዋሪያት ዘመን የተጨመሩ አማኞች አካቶ የክርስስቶስ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን እየተገነባችና በዓለም ሁሉ እየሰፋች ነው፡፡ ገና ወደፊትም ጌታ እስከ ሚመጣ ድረስ ብዙዎች የጌታ አካል በሆነችው ቤተ-ክርስቲያን ይጨመራሉ፡፡ ስለዚህ እያንዳንዳችን ለህንጻው መገንባት እንደጡብ ስፍራ እንይዛለን፡፡ ሙሉው ህንጻ የክርስቶስ አካል የአማኞች ስብስብ የሆነችው ቤተ-ክርስቲያንና

ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስን ነው። ሁላችንም ለአካሉ ግንባታ በተሰጠን ጸጋ እንሰራለን። ክርስቶስ ህይወቱን እስከ መስጠት ድረስ የወደደውን፣ የእርሱ መንፈስ ያለበትን ለአካሉ አንደ ጡብ የሆነውን ማንኛውም ክርስቲያን ዝቅ አድርጎ ማየት ጌታን ያሳዝናል።

በጌታ ያመኑት ሁሉ አንድ የሚያደርጋቸው ምንድነው፡-

ኤፌ 4፡4-6 አንድ ተስፋ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ አካልና አንድ መንፈስ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት ሁሉ በሁሉም የሚሰራ በሁሉ የሚኖር የሁሉ አባት የሆነ አንድ አምላክ አስተሳስሮናል።

ይህን በመረዳት ከጌታ የተነሳ ያገኘነው አንድነታችን እጅግ ልንጠነቀቅለት ይገባል።

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ. ም.